# የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳም

ከኃይለ ልዑል ግርማ (ዋሽንግተን ዲሰ)

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከፍተኛ ድጋፉን የሰጠውንና ብዙ መስዋዕትነት የከፈለበትን የቅንጅትን ፓርቲ በወያኔና የውጭ ኃይሎች ተባባሪ መሰሪነት አስቀድሞ ከውስጡ በተሰገሰጉ፣ ከዚያም በፍርሃትና በሆዳምነት አቋማቸውን በቀየሩ ደካሞች አማካኝነት ፓርቲውን የማዳከምና የማፈራረስ ስራ ከምርጫው መጭበርበር ጀምሮ እስካሁን ሲካሄድ ቆይኗል።

ለሰሚው ግራ የሚያጋባና ድጋፍ ሲሰጥ የነበረውን ደጋፊ ተስፋ አስቆርጦ እቤቱ እንዲቀመጥ ለማድረግ ያልተሞከረ ሴራ ተንኮልና ማጭበርበር አልነበረም። የሴራው መሪዎች አንድ ሰሞን እንደ ተዋናይ ሲታዩ ከርመው የመጡበት የተንኮል መንገድ ሲነቃባቸው ደግሞ ጥፍት ይሉና ሌሎችን ደግሞ እየላኩ በተመሳሳይ መንገድ ትግሉን በተሸናፊነት ለወያኔ ለማስረከብ የሚዳክሩ ሁሉ ቀፈታቸውን ከመሙላት በቀር በአገር ቤትም ሆነ በውጭው ያለው ኢትዮጵያዊ ማንነታቸውን እንዳወቀ ፊቱን ስለሚያዞርባቸው መልካቸውን እየቀያየሩ በመምጣት የትግሉን መሪ ለመያዝ ሲሞክሩ ይታያል።

በፖለቲካው መስክ ተሰማርተናል ከሚሉት አጠገብ ደግሞ የወያኔ ወኪሎች በኪነትንና በተለያዩ መስክ ባለሙያ ነን የሚሉ አድር ባዮችና ሆዳሞች ደግሞ የታወቁበትን ስማቸውን ለዘለዓለም ለማጥፋት ሲራወጡ እየተመለከትን ነው። ላያዋጣቸው ነገር ወያኔን ዘለዓለማዊ አድርገው ያገራችን ሕዝብ በስቃይና በመከራ በረሃብና በችግር እያለ "አገራችን ይህን ያህል ማደግዋን አላወቅንም ነበር" በማለት የወያኔ ባለጊዜዎች ዘርፈው ያካበቱትን ንብረት እንደ አገር ልማትና እድገት እየተመለከቱ የሚያናፍሱ ደካማ ፍጡሮችንም እየታዘብን ነው። ከእድሜም ከልምድም ከዝናም ሳያንሳቸው ሕዝባቸውን የካዱ ሁሉ ደግሞ ሕዝብ ክህደታቸውን በምን ዓይነት መንገድ እንደሚከፍላቸው ብዙም ሳይቆዩ ይረዱታል።

ወደ ዋና ጉዳዬ ልመለስ። ቅንጅትን ለመከፋፈል ከአናቱ ላይ ተቀምጠው የነበሩት ተዋንያኖች ምን ሲሰሩ እንደከረሙ ሰምተናል፣ ተመልክተናል። ሆኖም ግን ጥቂት ወራቶች አለፉና የተረሱ ይመስላል። እስቲ በጥቂቱ እናስታውስ እና ለምን ማንሳት እንዳስፈለገ ትረዳላችሁ።  ዛሬ አንዱ ቡድን በውጭ ያለውን ትግል ለማዳከምና ደጋፊውን ግራ ለማጋባት መለኪያና ጠርሙስ ታጥቆ፣ ላፕቶፕ አንግቦ፣ የፓልቶክና የዌብሳይት ሡራዊት ካድሬዎቹን አሰልፎ "ኢትዮጵያን ነጻ ላወጣ ድል ላደርግ ነው እቀፉኝ ደግፉኝ" በማለት እያሳቀን ሲገኝ፤ ሌላው ክፍል ደግሞ "የቅንጅት ወራሽ ነኝ ይገባኛል" እያለ አገር ቤት ያለውን ሕዝብ ሊያደነቁር ይሞክራል። ኸረ ለመሆኑ እነዚህ ሰዎች ዛሬ ምን ተዓምር ወርዶ ነው ልዩ ሆነው የቀረቡት? ትላንት ወያኔ ሲገባ አብረው የገቡ ከነመለስና ታምራት ላይኔ ጋር የውስኪ ብርጭቆ ሲያጋጩ በፎቶግራፍ ያየናቸው አይደሉምን? እነዚህ ሰዎች በወያኔ ከሥራው በተባረረው ምሁር ተተክተው ሲሰሩና በንግድ የከበሩ አይደሉምን? በወያኔ ሥርዓት የሰለጠኑ የተሾሙ አልነበሩምን? ቆራጥ ታጋዮች ቆላ ደጋ እየወረዱ ሕዝብ ሲያደራጁ ሲያስተምሩ ሲታገሉ እነርሱ በምቾት ከተማ ተቀምጠው አይናቸውን ጨፍነው ተቀምጠው አልነበረምን? ምርጫው ሲቃረብ ተጠቃቅሰው ፓርቲ መሰረትን ብለው የተደባለቁና ከአናት ቁጭ ብለው በሶስት ወር ዝናቸው ሰማይ ጥግ የደረሰ የሥልጣን ቋማጮች አልነበሩምን? በምርጫው ግርግር ከወያኔ ጋር በጎን እየሄዱ ሲደራደሩ የሕዝብን ሰላማዊ አመጽ ሲያከሽፉ አልነበር የታዩት? ከቃሊቲ እስር ቤትስ ሆነው አመራሩን በመከፋፈልና ደካማዎችን በመደለል ሴራ ሲጎነጉኑ የነበሩ መሆናቸውን ዘነጉትን?ከሕዝብ በፊት የአሜሪካ ደጋፊዎቻቸውና ምቾታቸውን አስበው አሰቀድመው ባዘጋጇቸው ሰዎች አማካኝነት የውጭውን ደጋፊ ከፋፍለው በሊሞ ሲንፈላሰሱና ጉሮ ወሸባዬ ሲደለቅላቸው ልባቸው ያበጠና በቅንጅት ስም ገንዘብ ሰብስበው ለራሳቸው ያደረጉት አይደሉምን? በኢትዮጵያ እስረኛ መቶ ብቻ ናቸው ያሉት ብለው የቀላመዱ፣ የትግራይን ሕዝብ በቅንጅት ስም ይቅርታ የጠየቁ ከሃዲዎች አይደሉምን? ታዲያ ቅንጅትን ለማፍረስና ለማጥፋት ዋና ተወናይ የነበሩት በምን ምክንያት ነው የቅንጅት ወራሽ ነን እያሉ እነ ወይዘሮ ብርቱካንና ፕሮፌሰር መስፍን የሚቀባጥሩት?

**ቅንጅት** እኮ ሰኔ 14 እና 15 ቀን 2000 ዓ.ም ከመላ ኢትዮጵያ የመጡ ተወካዮቹ ጠቅላላ ጉባዔ አድርገው ውሳኔ ወስነዋል፣ መሪዎቻቸውን መርጠዋል፣ የፓርቲውን ደንቦቹን አሻሽለዋል።  የቅንጅት አመራር የፓርቲው ስም ሲነጠቅ በፍርድ ቤት ከሶ ተሟግቷል። አላግባብ ቢፈረድበትም በይግባኝ ላይ

ይገኛል:: የስምንቱን ነጥቦች ጉዳይ ዛሬም የሚያነሳው የመጀመሪያው አብይ ነገር ነው::እንደ ነፕሮፌሰር መስፍን አባባል ግን 16 የቅንጅት ላዕላይ ምክር ቤት አባላት ማጆሪቲ ነው ይሉታል:: ወይ አለማወቅ ከ16ቱም አንጃዎች ወይም ከስድሳውም ላዕላይ ምክር ቤት በላይ ጠቅላላ ጉባኤው ሙሉ ሥልጣን ያለውና ከፍተኛው አካል መሆኑን ሳያውቁት ቀርተው ነውን? ወይዘሮ ብርቱካን እንዴ የብርሃኑ ነጋ አሻንጉሊት ስትሆን እርሱ ካገሩ ወጥቶ ሲቀር ደግሞ ፕሮፌሰሩ እርሷን ሊመሩ እርሷ ደግሞ የኢትዮጵያን ሕዝብ እንድትመራ የሚደረገው ምን ለማድረግ ነው? የኢትዮጵያን ሕዝብ መብትና ክብር መዳፈር መሆኑን እንዴት ተዘነጋቸው? በምን ሥልጣን ነው ፕሮፌሰሩ ብርቱካን ኢትዮጵያን ትምራ ተከተሏት የሚሉን? ሕዝብ እኮ የሚፈልገውን ያውቃል፣ ይመርጣል፣ ይከተላል:: አሜሪካ አገር ሽርሽር ላይ ከርመው ሲመለሱ ለቪኦኤ በሰጡት ቃለ መጠይቅ አሜሪካ የሄዱበት ምክንያት "የቅንጅት ወራሽነታችንን ለሕዝብ ለማስተዋወቅ ነው" ሲሉ አለማፈራቸው ይገርማል:: ቅንጅትንማ ፕሮፌሰር መስፍን ያኔ በታሰሩበት ጊዜ ጌታን እንደ ካደው እንደ ጴጥሮስ ሽምጥጥ አድርገው አልካዱትምን? እኔ ቅንጅት አይደለሁም ብለው በዚህ እድሜያቸው ክደው ዛሬ ደግሞ ወራሽ ነን ይላሉ:: ምነው ቅሌት በቅሌት ይሆናሉ. ትላንት የተናገሩትን ዛሬ እየካዱ:: ሌላ ፓርቲ እኮ መስርተናል ያላችሁ ጊዜ ቅንጅትን ጥላችሁ ሄዳችኋል:: እነ ብርሃኑ ነጋ በገንዘብ የደለሏቸውን ጥቂት ሰዎችን ይዛችሁ ለቅንጅት ስምና አርማ መከራከሩ ቀርቶ ምንም ዓይነት ጥያቄ ሳትጠይቁ እኮ ነው ሌላ ፓርቲ መስርተናል ያላችሁት:: ለነገሩ ያልወለደችውን ሕጻን ተቀርጦ ይሰጠኝ ካለችው ጨካኝ ሴት በምን ትሻላላችሁ ያልደከማችሁበት ስለሆነ ስሙ ለማንም ሲሰጥ ግዴላችሁም:: እናንተ አንድ ፓርቲ ያኛው ከሃዲ ደግሞ ሌላ ቡድን መሰረትን አላችሁ::

ዛሬ ደግሞ ቅንጅት ከበፊቱ በጠራና በተጠናከረ መልክ መነሳቱን ስትረዱ የቅንጅት ወራሽ ነን ምናምን ትላላችሁ:: "ኮሌክቲቭ ሊደርሽፕ" እያላችሁ ስታላግጡና "የሚያጋጫቸው የሥልጣን ሽኩቻ ነው" እያላችሁ ስትቀላምዱ ቅንጅትን ከማፍረስ ሌላ ምን የሰራችሁ መስሏችሁ ነው:: ፕሮፌሰር መሥፍን በተፈጥሮ የሌሎችን ሥራ በማናናቅና በሥራው ውጤታማ የሆነን ሰው ሁሉ በጥላቻና በቅናት መንፈስ ይመለከቱ እንደነበር እና ያ አብሮዎት ያረጀውን ክፉ ባህርይ በዚህ እድሜዎ መተው አቅቶዎት ለውርደት አበቃዎት:: ዛሬ ፓርቲ መስርተናል ካሉ በዚያው ግፉበት ቅንጅትን ግን ለቀቅ ያድርጉ::

አሁን ደግሞ የተጀመረ ጨዋታ አለ:: ከቅንጅት ጋር ተስማምቶ ለመስራት ለመዋዋል እያሰባችሁ መሆኑን ነው:: የእናንተ ሥራ የወያኔን እድሜ በተቃዋሚ ስም ማራዘም ስለሆነ ከቅንጅት ጋር መስማማት መተባበር አያስፈልጋችሁም:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ማን እንደሆናችሁ ያውቃልና በጀመራችሁበት መንገድ ቀጥሉበት:: ፕሮፌሰር መሥፍን በሰኔ ወር አካባቢ መስርተናል የምትሉት ፓርቲ መሪው ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ናቸው ሲሉ የተናገሩት በትክክለኛ አዕምሮዎ ነበር እንዲያ ያሉት? የፓርቲያችሁ ምስርታ እለት ኢንጂነር ኃይሉ ተገኝተው ንግግር እንዲያደርጉ ስታስቡስ ምን ማለታችሁ ነበር? እንዴት ለማጥፋት ለመግደል የምትፈልጉትን ፓርቲ መሪ ትብብር ፈለጋችሁ? አሁንም ቀልዳችሁን ተዉና በራሳችሁ ጎዳና ግፉበት:: ቅንጅት የኢትዮጵያ ሕዝብ ፓርቲ ስለሆነ ከሕዝብ ጋር እየመከረ ይሰራል:: እናንተ ፓርቲ የምትሉት ጥቂት አዲስ አበባ የተቀመጡ ተማርን የሚሉ ግለሰቦችን ነው:: የእናንተ ፓርቲ ከሕዝብ ፓርቲ በጣሙን የተለየ ነውና ምንም ዓይነት ሥራም ሆነ ውል ከእናንተ ጋር መዋዋል በጭራሽ አስፈላጊም አይደል:: አልሆነላችሁም እንጂ ቅንጅትን ወግታችሁታል፣ አድምታችሁታል ለመግደል ሞክራችኋል::ግን ቅንጅት አልሞተም:: ወ/ሮ ብርቱካን በኖረችበት በሰፈርዋ መኖር አለመቻልዋ በቁሚ ከመሞት ሌላ ምንን የሚያሳይ ይመስላችኋል? ስለሆነም ሕዝብ እንደጠላችሁ፣ እንዳልተቀበላችሁ ስታውቁትና ስትረዱት ተመልሳችሁ ለመግደል የሞከራችሁትን ቅንጅት ዛሬ እንዲያድናችሁ "ተስማምተን ተደጋግፈን እንስራ" የምትሉት ነገር ተቀባይነት አይኖረውም:: የቅንጅት መሪዎችም ዳግም አይታለሉም:: መግቢያው መውጫያው ጠፋባችሁ እንዴ? የሕዝብ ድጋፍ አለን አላላችሁም በጀመራችሁበት መንገድ ቀጥሉበት እንጂ:: ከብርሃኑ ነጋ ጋርም እንደለመዳችሁት በድብቅ መልዕክት እየተላላካችሁ እስከ 2010 ምርጫ ድረስ ቀጥሉበት:: የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደሆን በእናንተ እርሙን አውጥቷል:: የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳም አይደል ተረቱ:: ቅንጅት ደግሞ ዛሬ በጥራት ተጠናክሮ ቀጥሏል::

ቅንጅት የኢትዮጵያ ሕዝብ ምርጫ ነው!